# አብይ አህመድ ስልጣኑን ይልቀቅ!

አብይ አህመድ በጎሳ ፌዴራሊዝም በሚያስተዳድራት አገራችን ኢትዮጵያ ዜጎች በማንነት ተለይተው ይጨፈጨፋሉ። በግፍ የሚገደሉት ስጋቸው በሰው ይበላል፣ ወይም አስከሬን በየሜካው እንደትቢያ ይጣላል። መንግስት እያወቀ በተለይ በወለጋና በመተከል በየቀኑ ሰዎች ይገደላሉ። አገዛዙ በግፍ የተጨፈጨፉትን እውቅና አይሰጥም። ብሔራዊ የሀዘን ቀንም አያውጅም። ጭፍጨፋውን የመንግስት መገናኛ ብዙሃን አይዘግበውም። የሞቱትን ንፁህን እንደሰው በክብር አያስቀብርም። ህዝብ በየቀኑ ስጋት ላይ ነው፣ ዛሬን በሰላም ውሎ ስለማደሩ እርግጠኛ እንዳይሆን እየተሰራ ነው።

የኦዴፓ ባለስልጣናት በትእቢት ተወጣጥረው ፀረ ሰላም መርዝ የሆነ ንግግር በሚያደርጉበትና አንዳንዴም የመንግስት ባለስልጣናት ከገዳይ ጋር በጥምረት የሚሰሩ ከሆነ፣ የኦሮሞ ልዩ ኃይል ከ30 ዙር በላይ ያስመርቀውና ሊዩ ኃይሉ በተረኝነት ስሜት ህዝብ እንደሚያንሳቁሉና ለገዳይ ሽፋን እንደሚሰጡ ይታወቃል። ታዲያ እነእስክንድር ነጋን በግፍ ያሰረ፣ በአዲስ አባባ ህግ ጥሶ ታከለ ኡማንና አዳነች አበቤን በተረኝነት ከሌላ ቦታ አምጥቶ የሾመና አዲስ አበቤን የሚያጠቃ፣ የወያኔን ህገመንግስት አልቀይርም ያለው፣ የክልል ተብየዎቹን አወቃቀር ወጥነት ያለው ያላደረገው የአብይ ስልጣን ለኦሮሙማ ካልሆነ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያንና ምን ይሰራል?

አንደበት ከተግባር፣ ያልተገናኘበት

ሰብዓዊ ማንነት፣ በግፍ የጠፋበት

የሰው ደም በጅምላ፣ የሚገበርበት

የደም ብልፅግና፣ የኢትዮጵያ ውድቀት

የኦሮሞው ገዥ፣ ፍርድን ያዛባበት

የአብይ ሸንገላ፣ በቃን አለቅንበት

ይፈርበት አብይ፣ ለጠፋው ነፍስ ሁሉ

ስልጣኑንም ይልቀቅ፣ ይብቃ መሸንገሉ።

ዘውዲቱ የማነ

2020-12-28




